በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 212309

ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ጎሳ ፍቃዴ

2. አቶ ጉተማ ድሬሳ

3. አቶ አንዱአለም ታዬ ቤተሰብ የሆኑ ሻሚል ከማል ቀረቡ

4. ምርትነሽ አለሙ

5. ገነት ኤልያስ

6. እየሩስ ጅብሪል

ተጠሪ፡- በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የቀረበው በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 20704 ጥር 03 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02849/2013 ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00971/13 ሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ)፣ 37 እና 539/1(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ በጋምቤላ ከተማ 05 ቀበሌ ውስጥ ባሮ ማዶ ተብሎ በሚጠራበት አካባቢ በቀን 03/12/2012 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ 2ኛ አመልካች፣ የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ 3ኛ አመልካች፣ የሥር 5ኛ ተከሳሽ እና 5ኛ አመልካች በገነት ኤልያሥ ግሮሰሪ ከግል ተበዳይ ጋር አብረው መጠጥ ሲጠጡ የነበሩ መሆኑን፣ 1ኛ አመልካች ንብረትነቱ የፍቅር ፔንሲዮን የሆነውን ድርጅት ኃላፊ እና የጥበቃ ተቆጣጣሪ መሆኑን፣ 4ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ደግሞ የፍቅር ፔንሲዮን ሰራተኞች ሆነው በክሱ በተገለፀው ቦታ፣ ሰዓትና ቀን 2ኛ አመልካች፣ የስር 3ኛ ተከሳሽ፣ 3ኛ አመልካች እና የስር 5ኛ ተከሰሽ ሆነው በ3ኛ አመልካች ስልክ ወደ ግል ተበዳይ ስልክ ቁጥር በመደወል ወደ ፍቅር ፔንሲዮን ቤርጎ ቁጥር 2 በማስገባት ደብድበው በማነቅ እና በማፈን ከአልጋ ክፍል አውጥተው ወደ ጓሮ ወስደው የደበደቧት መሆኑንና የግል ተበዳይ የድረሱልኝ ጥሪ ስታሰማ የነበር መሆኑንና የግል ተበዳይን ልብስ አውልቀው ታርጋ ቁጥር በሌለው ባጃጅ አስከሬኑን ጭነው ወደ ኦፔኖ ቴክኒክና ሙያ አካባቢ ወስደው የጣሏት መሆኑን፣ ቤርጎ ቁጥር 2 ውስጥ የግል ተበዳይ የአንገት ጨሌ የተገኘ መሆኑን በመግለጽ 1ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ አመልካቾች የፍቅር ፔንሲዮን ሰራተኞች ሲሆኑ የግል ተበዳይ የድረሱልኝ ጥሪ ስታሰማ እየሰሙ ዝም በማለታቸው የዚህ ወንጀል ድርጊት አባሪ ተባባሪ መሆናቸውን፣ ሌሎች አመልካቾች ደግሞ በዋና ወንጅል አድራጊነት በፈጸሙት ጨለማን ተገን በማድረግ የከባድ ግፍ ግድያ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በስር 3ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮቻቸው የቀረበባቸውን ክስ አስተባብለውላቸዋል በማለት በነፃ የለቀቋቸው ሲሆን አመልካቾችን በሚመለከት ግን የግል ተበዳይ መሞታቸው በፎቶ ግራፍ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፣ ሟች የግል ተበዳይ ፍቅር ፔንሲዮን ውስጥ ስለመገደላቸው የዓ/ህግ ማስረጃ የሚያረጋግጥ መሆኑን፣ 1ኛ

አመልካች የድርጅቱ ጥበቃ ሆነው እየሰሩ በመሆኑ የሰዎችን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት እያለባቸው ዝም በማለት ከገዳዮች ጋር አብረው ስለመሆናቸው የሚያስረዳ መሆኑን፣ 4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ደግሞ በድርጅቱ ውስጥ ወንጀል ተሰርቶ እያለ ለሚመለከተው አካል አለማሳወቀቸው የወንጀሉ ድርጊት ተባባሪ መሆናቸውን የሚያሳይ መሆኑን በመግለጽ ከ1-3 ድረስ የተዘረዘሩት አመልካቾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ከ4-6 ያሉትን አመልካቾች ደግሞ በአባሪ ተባባሪነት ጥፋተኛ በማለት ከ1-3 የተጠቀሱትን አመልካቾች በ 25 ዓመት ጽኑ እስራት፣ ከ4-6 ያሉትን አመልካቾች ደግሞ በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና በክልሉ ሰበር ችሎት ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 03/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌና የተከሰሱበት የወንጀል ፍሬ ነገር የማይገናኝ መሆኑን፣ ሟችን የገደሉበት መሳሪያ ሳይገለጽ፣ ሟችን ለመግደል አመልካቾች ምንም ዓይነት ሀሳብ እንዳላቸው ሳይረጋገጥ በደፈናው የተጠሪ ማስረጃዎች በበቂ ሁኔታ ሳያስረዱ የስር ፍ/ቤት ጥፋተኛ በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ 2ኛ አመልካች ለሟች ስልክ ድውሏል በሚል ብቻ ዋና ወንጀል አድራጊ ተብለው የተቀጡ መሆኑንና ከኢትዮ ቴሌኮም የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣ የመ/ምስክሮች በደንብ ያልታዩላቸው መሆኑን፣ አመልካቾች ከሟች ጋር አብረው ያልነበሩና ሟች ሌላ ሰው ጋር የነበሩ መሆኑን፣ የዓ/ህግ ምስክር ጨለማ በመሆኑ ገዳዮችን ያለዩዋቸው መሆኑን፣ ቅጣቱም የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን ያልተከተለ መሆኑን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነትን ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን ጥቅምት 19/2014 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት በዓ/ህግ የቀረበው የወንጀል ክስ በሰውና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ከጥርጣሬ በላይ የተመሰከረባቸው ስለሆነ በተጠቀሰው የወንጀል ህግ ውሳኔ መሰጠቱ ትክክል መሆኑን፣ የዓ/ህግ የወንጀል ማመልከቻ በወንጀል ህግ ቁጥር 23 መሰረት የተሟላ መሆኑን፣ የዓ/ህግም ሆነ የአመልካቾች ምስክሮች በሚገባ የተሰሙ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማት ተከራክሯል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ውሳኔ በተከሳሹ ነጻነት ወይም ሕይወት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በመሆኑ በተከሳሹ ላይ የሚቀርበው ክስ ተከሳሹ የወንጀሉን ድርጊት ስለመፈፀሙ ብቻ ሣይሆን ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ፣ወንጀሉ እንዴት እንደተፈፀመና ወንጀሉ በማን እንደተፈፀመ በዝርዝር መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግም በሚያቀርበው ማሥረጃ በክስ አቤቱታው ላይ የተገለፀው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመ ስለመሆኑ እና የወንጀል ድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት እና በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ሁኔታ የማስረዳት ሸክም (Burden of proof) እንዳለበት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 111፣ 141 እና 149 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ክሱን የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል የሚባለውም ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች ይዘት እርስ በእርሳቸው የሚፋለሱ ፍሬጉዳዮችን ያልያዙ፣ወጥነት ያላቸው ተደጋጋፊ እና ተመሣሣይ ጉዳይ ማሥረዳት የሚችሉ እና ተዓማኒነት ያላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችለውም ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ተከሳሹ ወንጀል መፈፀሙን እና ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ያስረዳ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2)እና(4)፣57፣58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ክስ አመልካች ሟችን ለመግደል ያነሳሳውን ምክንያት ያልጠቀሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤሕግ ክሱን ለማስረዳት በፍርድ ቤቱ ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ 1ኛ ምስክር በእለቱ ከ2ኛ አመልካች እና ፍሬው ከተባለ ሰው ጋር ሲጠጡ እንደነበር ምስክሩ ትቶአቸው ቀድሞ እንደሄደ፣ በማግስቱ 2ኛ አመልካች ደውሎ ከእኛ ጋር የነበረችው ሴት ሰው ገድሎታል ፖሊሶች ከያዙህ አትንዘባዘብ እንዳለው በመቀጠልም ወደ አዲስአበባ እንሂድ ስለእኔ ከተናገርክ እገድልሃለሁ እንዳለው የመሰከረ ነው፣ 2ኛ ምስክር ጩኸት ሰምቼ ስወጣ ድምጽ አለ ከፍ ተደርጎ የተከፈተ የሚዘፍነ ሞባይልም አለ ሟች የተገደለችበት ቦታ መብራት ነበር ደብዳቢዎቹን ግን ከሩቅ ቦታ ስለነበር አላየኋቸውም በማለት የመሰከረች ነች፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች ደግሞ ጩሌ በቤርጎ ቁጥር 2 ተንጠልጥሎ ያገኙ እና ጩሌውም የሟች መሆኑን በመግለጽ ከመመስከራቸው በቀር በእርግጥም በክሱ በተገለጸው ሁኔታ አመልካቾች የግድያ ወንጀሉን ሲፈጽሙ አይተናል በማለት የተሰጠ የምስክርነት ቃል የለም፡፡ ይህም ከመነሻውም ቢሆን ዓቃቤሕግ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ያላስረዳ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩ ወንጀል ከመሆኑ እና ተከሳሹ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በቂ እና አሳማኝ ሊባል በሚችል ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው ከመሆኑ አኳያ በፍቅር ፔንሲዮን ቤርጎ ቁጥር 2 የአንገት ጩሌ የተገኘ መሆኑን፣ 4ኛ አመልካች ለሟች ስልክ ደውሎ የነበረ መሆኑ እና 2ኛ አመልካች ለ1ኛው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የዓቃቤሕግ ምስክር ደውሎ ከእኛ ጋር የነበረችው ሴት ሰው ገድሎአታል ፖሊሶች ከያዙሁ አትንዘባዝብ ወደ አዲስአበባ እንሂድ ስለእኔ ከተናገርክ እገድልሃለሁ ማለቱ ብቻውን አመልካቾች በእርግጥም ወንጀሉን ፈጽመዋል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከመነሻውም ቢሆን አመልካቾች ክሱን እንዲከላከሉ ብይን መሥጠቱ አግባብ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ አመልካቾችን ክሱን መከላከል ሳይስፈልጋቸው ከተከሰሱበት ክስ በነጻ ማሰናበት ሲገባቸው በአመልካቾች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 20704 ጥር 03 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝን እና የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 02849 ጥር 13 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00971/13 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ከተከሰሱበት ክስ በነጻ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ አመልካቾች ከተከሰሰበት ክስ በነጻ የተሰናበቱ መሆኑን አውቆ አመልካቾችን በዛሬው ዕለት ከእሥር እንዲለቅ ታዟል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድም የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው፡፡
- በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በዚህ ችሎት የተሻረ መሆኑን እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም